# 9ኛ ትምህርት

ከነሐሴ 14-20 Aug 20 - 26

## የሱስ ችግራቸውን እየፈታ አገለገላቸው

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማር. 5:22 —43፣ 10:46—52፣ ዮሐ. 5:1—9፣ መዝ. 139:1—13፣ ማር. 2:1—12፣ ሐዋ. 9:36—42።

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-** "ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምስራች እየሰበከ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ እየፈወሰ በከተሞቹና በመንደሮቹ ዞረ" (ማቴ. 9:35)።

ሴትየዋ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን አባል ናቸው። ዕድሜያቸው ለጡረታ ቢደርስም እርሳቸው ግን አገልግሎት ከመስጠት ወደ ኋላ የማለት ምኞት ፈጽሞ የላቸውም። የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ለብዙዎች ህልፈት መንስኤ ከሆነው ኤችአይቪ/ ኤድስ ክለላ ለማግኘት አጥብቆ ይሻል። በቫይረሱ ወላጆቻቸውን ለተነጠቁ ህጻናት የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ--እጅግ አፋጣኝ መፍትሔ ከሚሹ አንገብጋቢ ችግሮች አንዱ ነው። በ1994-1995 ዓ.ም. ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር የፈጠሩት ጥምረት ህጻናቱን በሳምንት ለስድስት ቀናት መመገብ አስችሎአቸው ነበር። ይህ በ50 ህጻናት የተጀመረ ግብረ ሠናይ እንቅስቃሴ ከአሥር ዓመታት በኋላ ማለትም በ2004-2005 ዓ.ም. በቀን 300

ህጻናት ወደ መመገብ ደረጃ መሸጋገር ችሎአል። በየጊዜው እየታየ የመጣው ለውጥ መዋለ ህጻናት ለመክፈት የሚያስችሉ ሁናቴዎችን በማመቻቸቱ በአሁኑ ወቅት 45 ህጻናትን ተቀብለው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ሌሎች አገልግሎቶችን በመተመለከተ አድራ (ADRA) በመባል የሚታወቀው የአድቬንቲስት ግብረ ሰናይ ድርጅት ልዩ ልዩ አልባሳትን በመስጠት ድጋፍ ያደርግላቸዋል። በግቢያቸው የሚያመርቷቸው አትክልቶችና የበቆሎ እርሻ ሌላው የድርጅታቸው የገቢ ምንጭ ነው። ለህመምተኞች የህክምና እርዳታ ይሰጣሉ። ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ገቢ ይተዳደሩ የነበሩ ሴቶች ቀለል ያሉ የሙያ ሥልጠናዎች እንዲወስዱ በመደረጉ ተጨማሪ ገቢ ፈጥረው የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ኑሮ የሚያሻሽሉበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል። ይህ የየሱስን ፍቅር በተግባር መግለጽ የቻለ እንቅስቃሴ በስፍራው አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተከፍቶ አገልግሎት እንዲሰጥ መንስኤ ሆኗል። ቤተ ክርስቲያኗ አገልግሎት መስጠት ስትጀምር የአባላት ቁጥር አምስት የነበረ ሲሆን በ2004 ላይ ማለትም ከአራት ዓመት በፊት 160 ለመድረስ ችሏል። በእግዚአብሔር ቸርነት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የወላጅ ዐልባ ህጻናት ማሳደጊያ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ግንባታ

ከአራት ዓመት በፊት በመጠናቀቁ እነሆ ዛሬ የተሻለ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

ይህ እንቅስቃሴ ማኅበረሰባችን አጥብቆ በሚሻው ወይም ብርቱ ፍላጎት በሚያሳይበት ጉድለቱ ላይ የድጋፍ ሥራ መሥራት ምን ያህል ለክርስቲያኖች አስፈላጊ እንደሆነ በተጨባጭ ማሳየት የቻለ ታላቅ ምሳሌ ነው።

*እሁድ ነሐሴ 15* *Aug 21*

# ጣልቃ የሚገባ አገልግሎት

የሱስ እንደገና በጀልባ ተሻግሮ በቅፍርናሆም የባሕር ዳርቻ ሲደርስ ከጀልባ ወረደ። ደቀ መዛሙርቱ በዐሥር ከተማ የሱስን በተገናኘው፤ አጋንንት ያደረበት ሰው አስጨናቂ ሁኔታ አሁንም ግራ እንደተጋቡ ናቸው። እንደ ተለመደው ብዙ ሕዝብ ሊገናኘው በባሕሩ ዳርቻ ተሰበሰበ። ሰዎች ወደ የሱስ አጠገብ ለመሆን አብልጠው ይጋፉ ጀመር፡ ፡ ሆኖም በዚህ መሀል አስቸኳይ እርዳታውን የሚሻ አንድ መልእክት ደረሰው። በወቅቱ ከምኩራብ አለቆች አንዱ ፈልጎት ነበር።

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ማር. 5፡22-43። የሱስ የምኩራቡን አለቃ ለማገልገል ወደ ቤቱ እያመራ እያለ በመሃል ጣልቃ የገባበት ጉዳይ ምን ነበር? ለጉዳዩ የሰጠው ምላሽ ምን ይመስላል? በእቅድ የያዝነውን አገልግሎት የሚያስተጓጉል ሌላ አገልግሎት ጣልቃ ሲገባብን የምንሰጠው ምላሽ ምን ይመስላል? ከታሪኩ ምን ዓይነት ትምህርቶች እናገኛለን?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------

የየዕለቱ ሥራችን እንዲሁም የግልም ሆነ ማኅበራዊ ጉዳዮቻችን እጅግ ብዙ፣ ተደራራቢና ፋታ የማይሰጡ ከመሆናቸው አኳያ ማናችንም ብንሆን በዕቅድ የያዝነው ሥራ እንዲስተጓጎል አንፈልግም። ሆኖም በእቅድ የያዝናቸውን ሥራዎች ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ጣልቃ ገብ ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግን መዘንጋት የለብንም።

አንድ ሰው ምቹ ባልሆነ ቦታና ሰዓት እርዳታችንን ሽቶ ቢመጣ ነገሩ የሚያበሳጭ ሊሆንብን ይችላል። አንዳንዴ ምንም ይምጣ ምን እየሠራን ያለውን ነገር ለአፍታ እንኳ ለማቆም ፍላጎት ላይኖረን ይችላል። ሆኖም ፈልገን ሳይሆን መሆን ስላለበት ብቻ ከምንሠራው ታቅበን እርዳታችንን ሽቶ ለመጣው በጎ የምናደርግባቸው አጋጣሚዎች ምን ያህል ናቸው?

የሚገርመው--የተደራሾችን ፍላጎት ተንተርሰው የሚሰጡ በእቅድ የተያዙ አገልግሎቶችን አስተጓጉለው ጣልቃ የሚገቡ አጋጣሚዎች--ሰዎችን በተሻለ ለማገለገል የሚያስችል ታላቅ ዕድል ይፈጥራሉ። ሆኖም አብዛኞቻችን በዕቅድ የያዝነው አገልግሎት እንዲካብን ስለማንፈልግ እቅዳችንን በሚያስተጓጉል ማንኛውም ነገር መበሳጨታችን-

-ብሎም ከፊታችን ገለል እንዲል መሞከራችን ያለና የተለመደ ነው። ወደ የሱስ ስንመለከት አገልግሎት ከሰጠባቸው አጋጣሚዎች አንዳንዶቹ ጣልቃ ገብ እንጂ በዕቅድ የተያዙ አልነበሩም። ይህም ሆኖ የሱስ ያን የፍቅር አገልግሎቱን ሰጥቶአቸዋል። ነገሩን አጽንኦት ሰጥተን ካሰብንበት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉንን በርከት ያሉ ዕድሎች የምናገኘው በእነዚሁ ጣልቃ ገብ አገልግሎት ፈላጊዎች ነው። ቀደም ባለው ጥናታችን የመልካሙን ሳምራዊ ታሪክ ተመልክተናል። በዚያ ስፍራ የተገኘው ይህ ሰው ወዴት ይሄድ እንደነበርም ሆነ ምን ሊያደርግ አቅዶ እንደነበር ከቶ ማን ሊያውቅ ይችላል? ሆኖም አገልግሎት ጣልቃ ገባና ከጉዳዩ ገታው።

አንድ ሰው (በቅርቡ ወይም ለመጨረሻ ጊዜ) አጥብቆ እንደሚፈልጎ በመግለጽ *ሥራዎን* ወይም ጉዳዮን ያስተጓጎለው መቼ ነው? ምላሽዎስ ምን ነበር? በዕቅዳችን መሃል ጣልቃ ስለሚገባ አገልግሎት ተነጋገሩ።

*ሰኞ ነሐሴ 16* *Aug 22*

# ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ማር. 10:46—52፣ ዮሐ. 5:1—9። የሱስ በእነዚህ በሁለቱም ታሪኮች እነዚህን የተለያዩ ሰዎች ጥያቄ ሲጠይቅ ይታያል። እንዲህ ማድረጉ ለምን ይሆን?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------እነዚህ ሁለቱም ሰዎች የሚፈልጉት ምን እንደሆነ በግልጽ እየታወቀ የሱስ ግን ምን እንደሚፈልጉ ሲጠይቃቸው ይታያል። ያም ባይሆን እንኳ ለእነርሱ አንገብጋቢው ጉዳይ ምን ሊሆን እንደሚችል ከእርሱ የተሰወረ አልነበረም። ሆኖም የሱስ እነዚህን ጥያቄዎች በመጠየቅ ለሰዎቹ የነበረውን አክብሮት አሳይቶአል። እያደመጣቸው እንደ ነበር ያሳያቸው የሱስ ጆሮውን ለእነርሱ መስጠቱ --ሲታገሉት ለኖሩት የሰቆቃ ህይወት በፈውስ የተሞላ ተደራሽነት እንዳመጣላቸው አሳያቸው። አንዳንድ ሰዎች ከበድ ያሉ ጫናዎችን በውስጣቸው አምቀው ይይዛሉ። ታዲያ እነዚህን ችግሮቻቸውን ለሚያዳምጣቸው ሰው ማካፈል ሲችሉ ከቀድሞ ቀለል ያለ መረጋጋት ያገኛሉ። ምናልባት ከምንም ነገር በላይ የሆነ ሰው እንዲያናግራቸው፣ እንዲያደምጣቸው አጥብቀው የሚሹ ወገኖች የሉምን?

ለምርመራ ወደ ሐኪም ሄደው ዶክተሩ አንዴ ብቻ ወደ እርስዎ መልከት አድርገው የመድኃኒት ማዘዣ ጽፈው ቢያሰናብትዎ ምን ሊሰማዎ እንደሚችል ለጥቂት ጊዜ አሰብ ያድርጉ። ሐኪሙ እርስዎ በትክክል የሚፈልጉትን በእርግጠኝነት መገንዘባቸውን በመጠራጠርዎ "ዶክተሩ ምን እንደሚሰማኝ የጠየቁኝ ጥያቄ የለም። የልብ አመታቴንም ሆነ የደም ግፊቴን አልለኩም . . . " ማለትዎ አይቀርም። ከህክምና የምርመራ አተገባበር ሕጎች አንዱ "ሕክምና ከመጀመርህ አስቀድመህ ምርመራ አድርግ" ይላል።

ተመሳሳይ ጽንሰ ሀሳብ--ትኩረቱን በሕዝቦች ሁለንተናዊ ደኅንነት ላይ አድርጎ ችግራቸውን ለመንቀስ በሚሠራው የወንጌል አገልግሎት ዘርፍ መዋል ይኖርበታል። ብዙዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ከሞላ ጎደል ይህን እንደሚያቁ ሊሰማቸው ወይም በማኅበረሰባቸው ያሉ ወገኖችን ለማገልገል ምን መደረግ እንደሚኖርበት ግምታቸውን ሊያስቀምጡ ይችላሉ። ጉልበታችንን አስተባብረን ወደ ማኅበረሰባችን በማምራት ሰዎች በግልም ሆነ በጥቅል አጥብቀው የሚፈልጓቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ቀርበን

ስናናግራቸው ስለ እነርሱ እየተጠነቀቅን እንደሆነ ግንዛቤ ያገኛሉ። እኛም በማኅበረሰቡ ተደናቂነት ያለው አገልግሎት እንዴት መስጠት እንዳለብን የሚያስገነዝበን ፍንጭ እናገኛለን። ከዚህ በተጨማሪ አዳዲስ ጓደኞችንም እናፈራለን።

"የማኅበረሰብዎ አካል የሆኑን ሰዎች በግል ቀርበው መሰረታዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት እገዛዎን ባሳዩ ቁጥር እጅግ የከፋውን ተቃውሞ ማክሰም እንደሚችሉ አይዘንጉ። ክርስቶስ በምድር ይመላለስ በነበረበት ወቅት ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በግል እየተገናኘ ችግራቸውን ይፈታ ነበር። የሱስ በሄደበት ሁሉ ህክምናን ከአምላካዊው ቃል ያዋደደ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። እኛም የእርሱን ዱካ እየተከተልን በጎ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅብናል። የተራቡትን እንድንመግብ፣ የታረዙትን እንድናለብስ እንዲሁም ያዘኑትን እንድናጽናና ሥልጠና ወስደናል።' "–Ellen G. White, Welfare Ministry, p. 162.

አብዛኞቻችን ስለ ራሳችን ለመናገር እንብዛም ባንታማም ነገር ግን የተሻለ አድማጮች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

*ማክሰኞ* *ነሐሴ 17* *Aug 23*

# በጥልቅ የተሰወረው መሻት

ሰዎች ስለ ራሳቸው ከሚያውቁት በላይ የሱስ እንደ ጌትነቱ ስለ እነርሱ አብልጦ ያውቅ ነበር። የሱስ ሰዎች በወቅቱ ያስቡ ስለነበረው (ማር. 2፡8) ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የቀድሞ ታሪካቸውን ጭምር (ዮሐ. 4፡18) ያውቅ እንደ ነበር የሚያሳዩንን አያሌ መረጃዎች በወንጌል ላይ እናገኛለን።

የእግዚአብሔር ቃል በመዝ. 139፡1-13 ምን ይለናል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

የሱስ የሕዝቡን ፍላጎት ያውቅ እንደ ነበርና በዚያ መሰረት እንዳገለገላቸው በትናንቱ ጥናታችን ተመልክተናል። እርሱ ወደ ታች ወርዶ ከመጥመቂያው ስር አጥብቆ ይሻ የነበረውንም ልብ ያውቅ ነበር። ይህ እውነታ ሽባውን ሰው ሲፈውሰው ተስተውሎአል። በእርግጥ ላይ ላዩን የሚታየው አካላዊ ፈውስ አስፈላጊ ቢሆንም ደግሞም ሌላ የማይታይ በጥልቅ ተሰውሮ ያለ አለ። ለዚያ ነው--የሱስ አልጋውን ተሸክሞ እንዲሄድ ከመንገሩ አስቀድሞ "አንተ ልጅ፣ ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል!" (ማር. 2፡ 5) ያለው።

በማር. 2፡1-12 እንደምናነበው ይህ ሰው ከነበረበት በታች ምን እየተከናወነ ነበር? ከአገልግሎታችን ተደራሾች ሁሉ እንዲህ ያለው እንደ ጽኑ ችግር መታየት ያለበት ለምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

ይህ ሰው ከአካላዊ ፈውስ በላይ የሆነ ብርቱ ነገር እንደሚያስፈልገው የሱስ ያውቅ ነበር። “ህመምተኛውም ቢሆን ከአካላዊው ፈውስ በላይ ከኃጢአት ሸክም የመገላገል ምኞት ነበረው። የሱስን ብቻ ማየት ችሎ የበደል ይቅርታ ማረጋገጫ ከተቀበለና ከሰማይ ጋር ሰላም ከፈጠረ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በነበረበት ሁኔታ ቢኖር ወይም ቢሞት ደስተኛ ነበረ።” --Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 267.

አገልግሎት የምንሰጠው ማንኛውም ሰው ኃጢአት ያጎሳቆለው ፍጡር ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን እንችላለን። ይህ ማለት በየትኛውም ሁኔታ ላይ የሚገኙ ወገኖች--አምላካዊው ጸጋ፣ ስለ ደኅንነት የተሰጠውን ተስፋ፣ ምርጥ የሆነውን ሁሉ የሚመኙላቸው፣ የሚወዳቸውና የሞተላቸው አምላክ መኖሩን የሚገልጥ ዕውቀት ሊያገኙ የግድ ነው።

እግዚአብሔር እንደሚወድዶት ጠንቅቀው ስለ መረዳትዎና ስላገኙት ደኅንነት በሚሰማዎ ጥልቅ ስሜት ዙሪያ አሰብ ያድርጉ። በተመሳሳይ ሌሎችም የእርስዎ ተሞክሮ ባለቤት ይሆኑ ዘንድ እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ?

*ረቡዕ   ነሐሴ 18*   *Aug 24*

## ዶርቃ በኢዮጴ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ሐዋ. 9:36—42። ዶርቃ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች በአካባቢዋ፣ በኢዮጴ በተለከተች ጊዜ ምን አደረገች? “አማኞችንና መበለቶችን” (ቁ. 41) የሚለው ሀረግ ምን ያመለክታል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ዶርቃ የተግባር ደቀ መዝሙር ነበረች። “በኢዮጴ ጣቢታ የተባለች አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች” (ሐዋ. 9:36)። ይህ አባባል እንደሚከተለው ቢቀመጥስ?--“በ [የእርስዎን ከተማና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስም ይጻፉ] እነርሱም ዘወትር በትጋት በጎ ነገር እያደረጉና ድኾችን እየረዱ ይኖሩ ነበር” (ሐዋ. 9:36)።

በጥቅሱ “አማኞች” (ቁ. 41) ክርስትና የተቀበሉ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ሲገልጽ “መበለቶች” ግን የቤተ ክርስቲያን አባላትንም ሆነ አባል ያልሆኑትን ሊያካትት ይችላል። ዶርቃ ሁለቱንም አካላት እንዳገለገለች ይታመናል። የእርስዎ “ኢዮጴ” በቤተ ክርስቲያንዎ ቅጥር ውስጥም ሆነ ውጪ ሊሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያንዎ ቅጥር ላሉ

ወገኖች የሚደረግ ተደጋጋፊነት ያለው እንክብካቤ ብርቱ የወንጌል ማሰራጫ ዘዴ ነው (ሐዋ. 2፡42-47)። ይህ ሲሆን በውጭ ያሉ ሰዎች “እያችሁ-- ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅር!” ሊሉ ይችላሉ።

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ዮሐ. 13፡34-35፣ ዮሐ. 15፡12። በሦስቱም ጥቅሶች የምናገኘው ተመሳሳይ ትርጉም ያለው መልእክት ምንድን ነው? እንደ ቤተ ክርስቲያን እንከተለው ዘንድ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? አልፎ አልፎ ይህን መከተሉ አስቸጋሪ የሚሆነውስ ለምን ይሆን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

ከቤተ ክርስቲያንዎ ውጪ ያሉ ሰዎችን ለማገልገል ዕቅድ ሲያወጡ ምን ዓይነት አነጋገር ወይም አቀራረብ መጠቀም እንደሚኖርብዎ ነገሩን አስቀድመው ማጤን ይኖርቦታል።

ኤሚ ሸርማን ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰብዋ አገልግሎት መስጠት ስለምትችልባቸውን ሶስት ዓይነት ዘዴዎች እንደሚከተለው ያብራራሉ። (1) አሰፋፈርን የተከተለው ዘዴ፡-- ይህ ዘዴ በቤተ ክርስቲያንዎ አካባቢ የሚገኙ ወገኖችን መሰረታዊ ችግር ለይቶ በመመልከት የሚሰጥ አገልግሎት ነው። እዚህ ላይ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ አገልግሎት የሰጡት ሴት በአቅራቢያቸው የሚገኘውን ማኅበረሰብ የእርሳቸው “ኢዮጴ” አድርገው መውሰዳቸውን ልብ ይሏል። (2) የአትክልተኛው ዘዴ፡-- አትክልተኞች የአትክልታቸውን ስፍራ ለቤታቸው ተጨማሪ ድምቀት የሚሰጥ የመኖሪያቸው አካል አድርገው እንደሚቆጥሩ--ከቤተ ክርስቲያንዎ ትንሽ ራቅ ብሎ ከሚገኝ ማኅበረሰብ ጋር ትስስር በመፍጠር የአገልግሎትን አድማስ ማሳደግ። አያሌ ቤተ ክርስቲያኖች ከሚገኙባቸው ማኅበረሰቦች ራቅ ብለው--አንዱ ከሌላው አጥቢያ ጋር በሚፈጥረው ኅብረት ማኅበረሰብ አቀፍ የአገልግሎት ማዕከል ማቋቋም የተለመደ ነው። ይህን ተከትሎ በአንድ ከተማ ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች የጤና ምግብ መሸጫ ሱቆች ይከፍታሉ። ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በአካባቢው አዲስ ቤተ ክርስቲያን ይጸነሳል። (3) የእረኛው ዘዴ፡-- ይህ ዘዴ በተለይ አንድ አካባቢ ወይም መልክአ ምድር ላይ ያለመ ሳይሆን በእቅድ የተያዘ ማኅበረሰብ ላይ ያተኮረ ነው።–Adapted from Ronald J. Sider et al., Churches That Make a Difference: Reaching Your Community with Good News and Good Works (Grand Rapids, Mich.: Baker Books, 2002), p. 146.

የማኅበረሰብዎን ችግሮች አንድ ባንድ ነቅሰው ለማውጣት የሚያስችሉትን የሥራ ሂደት ሲያስቡ--ይህማ ብዙ ጊዜና መሥዋዕትነት ይጠይቃል ሊሉ ይችላሉ። ስለዚህ አቋራጭ አካሄዶችን ለመጠቀም እንመርጣለን። ከላይ በጥቅሶቹ የቀረቡት ሁለት ተምሳሌታዊ ታሪኮች የወንጌልን ተልዕኮና የደቀ መዝሙርነትን ኃላፊነት እንደ ዋዛ አሳንሰን መመልከት እንደሌለብን ያስጠነቅቁናል። ጥናትና ምርምር ማድረግና ዕቅድ

*ሐሙስ ነሐሴ 19* *Aug 25*

## በሥራ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን

“የምታደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤ ዕቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል” (ምሳ. 16፡3)።
ቤተ ክርስቲያንዎ ማኅበረሰብዎን እንዴት ማገልገል እንደምትችል አስመልክቶ አንዴ ግልጽ ሆኖ የቀረበው ራዕይ ባለቤት ከሆነች በኋላ ይህን ራእይ ወደ ተግባር ለመለወጥ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን የሥራ ዘርፎች በአንድነት መሥራት ይችላሉ። ምንም እንኳ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ራስዎን እንደ “መሪ” ላይመለከቱ ቢችሉም የበኩልዎን አስተዋጽኦ ማበርከት ግን ይችላሉ። ደግሞም ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ይህን የእርስዎ ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ ያላትን ተልዕኮ አመልካች ሂደት ማስተዋላቸው መልካም ነው።

ቤተ ክርስቲያን የምታወጣው ዕቅድ ቢያንስ ከሶስት ምንጮች የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል። (1) ከመጽሐፍ ቅዱስና ከትንቢት መንፈስ መርኅዎች፤ (2) ማኅበረሰቡ አጥብቆ በሚፈልገው ነገር ላይ በተመሰረተ ዕውቀት (3) ምዕመኑ በሚሰጣቸው ግብአቶች። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች በወንጌል ተልዕኮ እንዴት ወደ ሌሎች መድረስ እንዳለባቸው እና በዚያው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት እንዴት መሻሻል እንዳለበት የሚመክር የሀሳብ ልውውጦችን ለማድረግ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን አባላት ይጋብዛሉ።

በሉቃስ 14፡25-35 ላይ የምናገኘው መልእክት የቤተ ክርስቲያንዎን ተልዕኮ ለማሳካት ሊከፈል ስለሚገባ መሥዋዕትነትና ስለ ዕቅድ አወጣጥ ምን ይነግረናል?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------

ለጌታ መስጠት ይኖርብናል። ይህን ካደረግን የምንሰጠውም አገልግሎት በቅንአትና በታማኝነት የተሞላ ይሆናል። በቅድሚያ ከቤተ ክርስቲያንዎ ጋር የማደራጀትና ዕቅድ የማውጣት ክንውኖችን በመተግበር ወደ ማኅበረሰብዎ ለመድረስ በበለጠ ለመሥራት የሚችሉባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

*አርብ ነሐሴ 20* *Aug 26*

## ተጨማሪ ሀሳብ

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ዘዳ. 15፡11፣ ኢዮብ 29፡11—17፣ ምሳ. 14፡31፣ 19፡17፣ ሐዋ 3፡6፣ ያዕ. 1፡27—2፡5። Ellen G. White, “Pioneering in Australia,” pp. 327—338, in Welfare Ministry.

እንደ የሱስ ሁሉ ጳውሎስም በግልጽ ይስተዋሉ ለነበሩ የሕዝቡ ችግሮች መፍትሔ ያመጣ ነበር። ጳውሎስ በአቴንስ ያቀረበው ታሪክ ለዚህ እንደ አብነት መጠቀስ ይችላል። በሐዋ. 17፡23 እንደምናነበው ሐዋርያው በከተማዋ ውስጥ የተመለከተው አንድ የጣኦት መሠዊያ የፈጠረበት ስሜት በአካባቢው ከነበሩት ምሑራን ጋር

እንዲሁም ከማንኛውም በገበያው ስፍራ ከነበረ ሊያዋራው ከሚችል ሰው ጋር ውይይት እንዲያደርግ መንገድ ከፍቶለት ነበር። ጳውሎስ የአቴንስ ነዋሪዎች የጎደሏቸውን ነገሮችና ችግሮች ለይቶ መመልከት ችሎ ነበር። “ለማይታወቅ አምላክ” የሚል ስያሜ የሰጡት መሠዊያ በሕይወታቸው ላይ የፈጠረው ክፍተት-- እውነተኛውን አምላክ ለማወቅ ፍላጎት እንዲኖራቸውና ከንቱውን የጣኦት አምልኮ እንዲያቆሙ መንስኤ ነበር። ከዚያም ጳውሎስ አይሁዶች “እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ግሪኮች” (ሐዋ. 17፡17) ጋር በአንድነት አምልኮ ያደርጉበት ወደ ነበረው ምኩራብ በማምራት መስበኩን ተያያዘው። በሌላ አነጋገር ይህን ያመቻቸውን ምርጥ ዕድል ወንጌልን ለማሰራጨት ተጠቀመበት።

ጳውሎስ በምኩራብም ሆነ በጎዳና ላይ ሕዝቡን እየተገናኘ ያናገረበትን ዘዴ ስንመለከት ሁሉም ባሉበት ለመድረስ የነበረውን ምኞት እናያለን። አቴናውያን “ለማይታወቅ አምላክ” (ሐዋ. 17፡23) የሚለውን መሠዊያ ማቆማቸውን ተከትሎ አብዛኛው ሕዝብ በዚህ ከተለመደው ለየት ባለ በማይታወቅ አምላክ ያምን ነበር፡ ፡ ጳውሎስ ይህን መነሻ ሀሳብ ይዞ “ ‘እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እገልጽላችኋለሁ’ ” (ሐዋ. 17፡23) በማለት ወደ እግዚብሔር ሊያመላክታቸው ተመኘ። ሐዋርያው በዚህ ሳያቆም ከራሳቸው ባለ ቅኔ አንዱ “ ‘ እኛ ደግሞ ልጆቹ ነን’ ”ሲል የጻፈውን እውነትነት ያለው መልእክት ሲጠቅስላቸው ይስተዋላል። እነዚያ ሕዝቦች ይገኙበት ከነበረው ነባራዊ ሁኔታ የተነሳው ጳውሎስ ከጣኦቶቻቸው አርቆ ወደ ሕያው እግዚአብሔርና ከሙታን ወደ ተነሳው የሱስ ሊመራቸው ፈለገ። በአጭሩ--ወንጌልን ለማሰራጨት በቅድሚያ የሕዝቡን ፍላጎት አቅጣጫ የገመገመው ጳውሎስ በመቀጠል እነዚያን ጉድለቶች የመሙላት ሥራ ለመሥራት ሞከረ።

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ሰላምና ደስታ እንዴት ወደ እነርሱ ሊሰርጽ እንደሚችል ያስተማራቸው ጌታ--ለጊዚያዊው አንገብጋቢ ችግራቸውም ሆነ ለመንፈሳዊ ጉዳዮቻቸው አሳቢና ተቆርቋሪ ነበር።”-Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 365. የሌሎችን ችግር እየነቀስን አገልግሎት ልንሰጥ የሚገባ ከመሆኑ አኳያ ከመልእክቱ ምን ዓይነት ጠቃሚ ሀሳብ እናገኛለን?

2. ወንጌልን ወደ ሌሎች ስለ ማሰራጨት ስናስብ የመጨረሻውን ግባችንን ምንነት እንዳንረሳ መጠንቀቅ የሚኖርብን ለምንድን ነው? ለመሆኑ የመጨረሻው ግባችን ምንድን ነው? ለመልስዎ ምክንያቶችዎን ያቅርቡ።

3. በአገልግሎት መሃል ሊገጥሙ የሚችሉን አንዳንድ ጣልቃ ገብ ክስተቶች እንደሚያበሳጩ ሳይሆን እንደ ተቀደሱ ዕድሎች መቁጠርን እንዴት መማር

እንችላለን? በዚህ ዙሪያ ገላ. 2፡20 እንዴት ይረዳናል?